የሰ/መ/ቁጥር 237911
ጥቅምት 02 ቀን 2016ዓ/ም

ዳኞች ፡- ተፈሪ ገብሩ(ዶ/ር)

እንዳሻው አዳነ

ተሾመ ሽፈራው

መላኩ ካሳዬ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች፡- ወ/ሮ ወይዙ አባተ አልቀረበም

ተጠሪዎች ፡- 1ኛ. አቶ አበበ አሼቦ } አልቀረበም

2ኛ. ወ/ሮ ኪቦ ኤምቤሎ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ የባልና ሚስት የንብረት ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የሰበር ቅሬታ የቀረበው የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 19170 በነሐሴ 10 ቀን 2014 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ነው ፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት ሀዲያ ዞን አንሌሞ ወረዳ ፍርድ ቤት የአሁን አመልካች ከሳሽ፤ 1ኛ ተጠሪ ተከሳሽ እና 2ኛ ተጠሪ ጣልቃ ገብ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

አመልካች በታህሳስ 01 ቀን 2012 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት ክስ ከ1ኛ ተጠሪ ጋር የነበረን ጋብቻ በፍቺ የፈረሰ በመሆኑ ሌሎች ንብረቶችን ጨምሮ እዚህ ሰበር ድረስ አከራካሪ የሆኑትን በጋብቻ ውል የተቆጠረልኝ 80 ቅጠል

ቆርቆሮ ቤት እና ከውጪ ሀገር በዌስተርን ዩኒየን በኩል ባንክ እንዲቀመጥ ለ1ኛ ተጠሪ የላኩትን 5930.28 የአሜሪካን ዶላር እንድካፈል ይወሰንልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

1ኛ ተጠሪ በጥር 06 ቀን 2013 ዓ.ም በሰጡት መልስ የወላጅ አባቴ ንብረት በሆነው 80 ቅጠል ቆርቆሮ ቤት ላይ የጋራ ንብረት እንዲሆን ከአመልካች ጋር የጋብቻ ውል ተዋውለናል፡፡ ይህን ያደረኩትም አመልካችን ለማግባት ካለኝ ፍላጎት የተነሳ እንጂ ንብረቱ የራሴ ሆኖ አይደለም፡፡ በራሴ ስም በሌለ ንብረት ላይ በመዋዋላችን ብቻ የጋራ ሊሆን አይችልም፡፡ ከውጭ ሀገር የተላከውን ገንዘብ ለአቶ አበራ ፉጋታ ሰጥቻለሁ፡፡ ሌላው ገንዘብ በአደራ የተላከ ሳይሆን ለጋራ ጥቅማችን የተላከ በመሆኑ ለትዳር ጥቅም ውሏል በማለት ተከራክረዋል፡፡ 2ኛ ተጠሪ ጣልቃ በመግባት ባቀረቡት ክርክር 80 ቅጠል ቆርቆሮ ቤት እና ይዞታው የኔና የባለቤት ሀብት ነው፡፡ በሌላ ሶስተኛ ወገን ንብረት ላይ የተደረገ የጋብቻ ውል አግባብነት የለውም፡፡ በመሆኑ ቤቱና መሬቱ አይመለከታቸውም ተብሎ ይወሰንልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው ፍርድ ቤት የግራቀኙን ምስክሮች ሰምቶ 1ኛ ተጠሪ በጋብቻ ውል ከአመልካች ጋር የጋራ እንዲሆን የተስማሙበት ቤት እና ይዞታ በ1ኛ ተጠሪ ስም የሚገኝ አይደለም፡፡ የጋራ ሊሆን የሚችለው ባለይዞታዎቹ ፈቅደው ለመተዳደሪያ እንዲሆን ሰጥተናል ቢሉ ነበር፡፡ በመሆኑም ባለይዞታዎቹ ፈቅደው ያልሰጡትን ቤት እና ይዞታ አመልካች ሊካፈሉ አይገባም፡፡ በሌላ በኩል አመልካች ከአረብ ሀገር የላኩትን ገንዘብ በተመለከተ 1ኛ ተጠሪ ለሌላ ሰው የሰጡ ስለመሆኑ ያቀረቡት ማስረጃ ስለሌለ ብር 5054 1ኛ ተጠሪ እና አመልካች እኩል ሊካፈሉ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለሀዲያ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ጠይቀዋል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍርድ ቤት ግራቀኙን አስቀርቦ ካከራከረ በኋላ ቤቱን በተመለከተ የስር ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ተገቢ ነው፡፡ አመልካች ለ1ኛ ተጠሪ በአሰሪዋ በኩል የላከችው ገንዘብ በተመለከተ 4886.60 ዶላር ለመሆኑ ማስረጃ ቀርቦ እያለ የስር ፍርድ ቤት ተገቢውን ማጣራት ሳያደርግ ብር 5054 እንዲካፈሉ መወሰኑ ስህተት ነው፡፡ በመሆኑም 4886.60 ዶላር በወቅታዊ የባንክ ምንዛሪ ተሰልቶ ግማሹን 1ኛ ተጠሪ ለአመልካች ይክፈሉ በማለት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ አሻሽሏል፡፡

1ኛ ተጠሪም በበኩላቸው በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ ይግባኙን ባለመቀበል የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን በማፅናቱ በመቀጠል ቅሬታቸውን ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበዋል፡፡ አመልካችም በጋብቻ ውል የተቆጠረው 80 ቅጠል ቆርቆሮ ቤት ሊካፈሉ አይገባም መባሉን በመቃወም መስቀለኛ የሰበር ቅሬታ አቅርበዋል፡፡ ሰበር ችሎቱ መስቀለኛ የሰበር አቤቱታው የከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ በሰጠ በ90 ቀን ውስጥ አልቀረበም በሚል ሳይመረምር አልፏል፡፡ 1ኛ ተጠሪ አመልካች የላኩትን ገንዘብ ለትዳር ጥቅም አውየዋለሁ በሚል ያቀረቡትን መከራከሪያ በሚመለከት 1ኛ ተጠሪ በሚገባ አላስረዱም፡፡ በአንጻሩ አመልካች ገንዘቡ ለትዳር ጥቅም አለመዋሉን ባቀረቡት ማስረጃዎች አስረድተዋል፡፡ በመሆኑም 1ኛ ተጠሪ ገንዘቡ ለትዳር ጥቅም የዋለ ነው በሚል የሚያቀርቡት መከራከሪያ ተቀባይነት የለውም፡፡ ሆኖም አመልካች ገንዘቡን የላኩት በ2006 እና 2007 ሆኖ እያለ 4886.60 ዶላር በአሁን ወቅት ባለው ምንዛሪ 1ኛ ተጠሪ ያክፈሉ መባሉ አግባብ አይደለም፡፡ በመሆኑም አመልካች የላኩት 4886.60

ዶላር ገንዘቡ በተላከበት ወቅት ባለው ባንክ ምንዛሪ ተመንዝሮ 1ኛ ተጠሪ ግማሹን ለአመልካች እንዲያካፍሉ ሲል በማሻሻል ወስኗል፡፡

አመልካች በህዳር 27 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር ቅሬታ በጋብቻ ውል ላይ 80 ቅጠል ቆርቆሮ ቤትና አራት ጥማድ መሬት በመተዳደሪያነት ሲመዘገብ  የተጠሪ አባትና እናት ይዞታውንና ቤቱን 1ኛተጠሪ እራሱ የሰራ መሆኑን በሽማግሌዎች ፊት አረጋግጠዋል፡፡ 2ኛ ተጠሪ በጊዜው ውል እንዲፈርስ ተቃውሞ አላቀረቡም፡፡ 4886.60 ዶላር ፍርዱ ካረፈበት ጊዜ ጀምሮ ባለው የባንክ ምንዛሪ መከፈል እያለበት በተላከበት ጊዜ በነበረው የባንክ ምንዛሪ ተሰልቶ ይከፈል መባሉ ተገቢ አይደለም፡፡ በመሆኑም የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ ይሻርልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

የአመልካች ቅሬታ በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ አመልካችና ተጠሪ በጋብቻ ወቅት አከራካሪው ቤትና ይዞታ የባልና ሚስቱ የጋራ እንደሚሆን በጋብቻ ውል የተስማሙ መሆኑ ባልተካደበት ሁኔታ የ2ኛ ተጠሪ ነው ተብሎ የተወሰነበት አግባብ መጣራት አለበት በማለት ተጠሪዎች መልሳቸውን እንዲያቀርቡ አዟል፡፡

1ኛ ተጠሪ በየካቲት 20 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት መልስ የገጠር የእርሻ መሬትና ቤት የባልና ሚስት የጋራ ንብረት አይደለም በሚል የተሰጠው ውሳኔ ህግን መሰረት ያደረገ ነው፤ አመልካች በጋብቻችን ዘመን በጋራ ያላፈራነውን የሌላ ሶስተኛ ወገን ንብረት ለመካፈል የሚያስችላቸው የህግ መሰረት የለም፤ የገጠር እርሻ መሬትና ቤት ህጋዊ ባለ ይዞታ 2ኛ ተጠሪና ባለቤታቸው አቶ አሼቦ ጃኪር ናቸው፤ ባልና ሚስት ጋብቻቸውን በሚፈፅሙብት ጊዜ በጋብቻቸው ውል የጋራ መተዳደሪያ እንዲሆን በውል ስምምነት መፈፀም የሚችሉት ከጋብቻው በፊት በየግላቸው የነበረውን የግል ንብረታቸውን እንጂ በሌላ ሶስተኛ ወገኖች ላይ ግዴታን የሚስከትል ስምምነት ማድረግ አይችሉም፡፡ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን የገጠር የእርሻ መሬትና ቤት 1ኛ ተጠሪ ከወላጆቼ በስጦታም ሆነ በውርስ ያላገኘሁት፤ በገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቃም አዋጅ ቁጥር 110/99 በሚያዘው መሰረት ለአንድም ቀን ተጠቅሜ የማላውቀው፤ መተዳደሪያዬ የመንግስት ስራ የሆነ እና አመልካችና 1ኛ ተጠሪ ክርክር ባስነሳው ይዞታ ላይ ለአንድ ቀን ኖረንም ሆነ ተጠቅመን የማናቀው ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤትም ይህንን በሚገባ አጣርቶ ሌላ መተዳደሪያና ገቢ የሌላቸውን 2ኛ ተጠሪ ከህጋዊ ይዞታቸው ላይ የማያፈናቅል ውሳኔ መስጠቱ ህጉን ተከትሎ መወሰኑን ያሳያል፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ሊጸና ይገባል ብለዋል፡፡፡፡

2ኛ ተጠሪ በበኩላቸው በየካቲት 20 ቀን 2015 ዓ.ም በሰጡት መልስ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካች ያቀረቡት አቤቱታ በህጉ የተቀመጠው ጊዜ ካለፈ በኃላ የቀረበ ነው ብሎ ውድቅ ያደረገውን ለዚህ ለሰበር ሰሚ ችሎት መቅረቡ የህግ መሰረት የለውም፡፡ ተጋቢዎች የሚያደርጓቸው ውሎች አስገዳጅ የህግ ድንጋጌዎችን የማይቃረኑና በሌሎች 3ኛ ወገኖች ላይ ግዴታን የሚያስከትሉ ሊሆኑ እደማይችሉ የተሻሻለው የፌዴራል የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀፅ 42 (1-3) እን አንቀፅ 47 (1) እንዲሁም የደቡብ ክልል ቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 75/96 አንቀፅ 51 (1-3) እና አንቀፅ 55 (1) ይደነግጋል፡፡ ተጋቢዎች የጋብቻቸውን ውጤት ሲወስኑ ተፈፃሚነት የሚኖረው የጋብቻ ውሉን አስገዳጅ የህግ ድንጋጌዎች እስካልተቃረነ ድረስ ብቻ ነው፡፡

ንብረቱ በሟች ባለቤቴ ስም ተመዝግቦ የመንግስት ግብር እየከፈልን የምንጠቀምበትና የምንተዳደርበት ህጋዊ ይዞታ ላይ ምንም አይነት መብት የሌላቸው አመልካችና 1ኛ ተጠሪ ንብረቱን የጋብቻ መተዳደሪያ በማድረግ መስማማታቸው ከህግ ውጪ ነው፡፡ አመልካችና 1ኛ ተጠሪ አርሶ አደርና የገጠር ነዋሪዎች አይደሉም፡፡ ትዳር የመሰረቱት በከተማ ሲሆን 1ኛ ተጠሪ መተዳደሪያው የመንግስት ስራ ነው፡፡ አመልካችም አረብ ሀገር ነበረች፡፡2ኛ ተጠሪ ምንም አይነት መተዳደሪያና አማራጭ መሬት የሌለኝ በመሆኑ ህጉ-ወጥ ውልን መሰረት በማድረግ መብቴን ለማሳጣት የቀረበውን ክስ የስር ፍርድ ቤት ውድቅ ማድረጉ ተገቢ ነው ብለዋል ፡፡

አመልካች በመጋቢት 20 ቀን 2015 ዓ.ም የተጻፈ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

የክርክሩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም ያስቀርባል ሲባል የተያዘውን ጭብጥ ከመመርመራችን በፊት የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ለክርክሩ መሰረት በሆነው ቤት ላይ አመልካች ያቀረቡትን መስቀለኛ የሰበር ቅሬታ ሳይመረምር ያለፈበትን አግባብ ከተገቢው ህግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው አመልካች ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን 80 ቅጠል ቆርቆሮ ቤት እና ይዞታ በጋብቻ ውል በ1ኛ ተጠሪ የጋራ ስለተደረገልኝ ልካፈል ይገባል በማለት ጠይቀው በጋብቻ ውል ላይ የጋራ ተብሎ ቢቆጠርም ቤት እና ይዞታው በ1ኛ ተጠሪ ስም የሚገኝ ባለመሆኑ የጋብቻ ውሉ ተፈጻሚነት የለውም በሚል በዚህ ንብረት ላይ አመልካች ያቀረቡት የክፍፍል ጥያቄ ጉዳዩን በመጀመሪያ እና በይግባኝ በተመለከቱ ፍርድ ቤቶች ውድቅ ተደርጓል፡፡ ተጠሪ ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡትን ቅሬታ ተከትሎ አመልካች የተጠቀሰው ቤት እና ይዞታ ላይ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠውን ውሳኔ በመቃወም መስቀለኛ የሰበር ቅሬታ ሲያቀርቡ ሰበር ችሎቱ ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ የሰጠው በጥቅምት 12 ቀን 2014 ዓ.ም ሆኖ እያለ አመልካች የሰበር ቅሬታ በህጉ በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ ሳያቀርቡ 1ኛ ተጠሪ ባቀረቡት የሰበር ቅሬታ መነሻነት የማቅረቢያ ጊዜ ካለፈ በኋላ በሰኔ 30 ቀን 2014 ዓ.ም ያቀረቡት መስቀለኛ የሰበር ቅሬታ ሊመረመር አይገባም በማለት አልፎታል፡፡

በአንድ የይግባኝ ክርክር መልስ ሰጪ የሆነ ወገን በቀጥታ ይግባኝ ያላቀረበ ቢሆንም እንኳን ተገቢውን ዳኝነት ከፍሎ ለይግባኝ ክርክሩ በመልስ ሰጪነት ከሚያቀርበው ክርክር ጋር በፍርዱ ቅር የተሰኘበትን ጉዳይ በማቅረብ በይግባኝ ባይነትም ለመከራከር እንደሚችል እና መልስ ሰጪው የሚያቀርበው የይግባኝ ቅሬታ የማቅረቢያ ጊዜ በይግባኙ ላይ መልስ እንዲያቀርብ መጥሪያ በደረሰው በ30 ቀን ውስጥ ሊሆን እንደሚገባ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 340/1 እና 2 ስር ተመልክቷል፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሚመራበት የራሱ የሥነ-ሥርአት ህግ እስከ ሚያዝያ 19 ቀን 2015 ዓ.ም ድረስ ያልነበረው በመሆኑ የፍትሓ በንሔር ክርክሮች ሲመሩ የነበረው በፍ/ሥ/ሥ/ሕጉ መሰረት በመሆኑ መስቀለኛ የሰበር ቅሬታ አቀራረብን በተመለከተ የፍ/ሥ/ሥ/ሕጉ አንቀጽ 340 ተፈጻሚ ሲደረግ እንደነበር የሚታወቅ ነው፡፡ የደቡብ ክልል ሰበር ሰሚ ችሎትም የራሱ የሰበር ሥነ-ሥርአት ሕግ የሌለው ከመሆኑ አኳያ ችሎቱ የፍትሐብሔር ክርክሮችን ሊመራ የሚገባው በፍ/ሥ/ሥ/ሕጉ በተዘረጋው ስርአት መሰረት በመሆኑ መስቀለኛ የሰበር ቅሬታ አቀራረብን በተመለከተ ተፈጻሚ የሚሆነው የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 340 ድንጋጌ ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ ንዑስ

*ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

ቁጥር 2 መሰረት መስቀለኛ የሰበር ቅሬታ ማቅረቢያ ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው በአመልካቹ የሰበር ቅሬታ ላይ ተጠሪው መልስ እንዲሰጥ መጥሪያ ከደረሰው ቀን ጀምሮ በ30 ቀን ውስጥ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የአመልካች መስቀለኛ የሰበር ቅሬታ ጊዜው ካለፈበት በኋላ የቀረበ ነው ያለው በከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሳኔ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በመቁጠር መሆኑን የውሳኔው ግልባጭ ያሳያል፡፡ ነገር ግን ውሳኔ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ የሚቆጠረው በአመልካች የቀረበው የሰበር ቅሬታ በህግ በተቀመጠው የሰበር ቅሬታ ማቅረቢያ ጊዜ ውስጥ የቀረበ መሆን ያለመሆኑን ለማጣራት እንጂ መስቀለኛ የሰበር ማቅረቢያ ጊዜ መቆጠር የሚጀምርበትን ጊዜ የሚመለከት አይደለም፡፡ በመሆኑም የደቡብ ክልል ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካች ያቀረቡት መስቀለኛ የሰበር ቅሬታ በከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሳኔ የተሰጠበትን ቀን መነሻ በማድረግ ጊዜው ካለፈ በኋላ የቀረበ ነው ማለቱ የክርክር አመራር ግድፈት የተፈጸመበት ከመሆኑም በላይ ተገቢ ባልሆነ ምክንያት የአመልካች የሰበር ቅሬታ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ሳይመረመር መቅረቱ በኢ.ፌ.ድ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80/3/ለ ስር የተመለከተውን አመልካች በስር ፍርድ ቤቶች ተፈጽሟል የሚሉትን መሰረታዊ የህግ ስህተት በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት እንዲታረም የመጠየቅ እና የመዳኘት ህገ መንግስታዊ መብታቸውን የሚጥስ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10 መሰረት ተከታዩ ተወስኗል፡፡

## <u>ውሳኔ</u>

1ኛ. የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 19170 በነሐሴ 10 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1 መሰረት ተሻሽሏል፡፡

2ኛ. የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የአመልካች መስቀለኛ የሰበር ቅሬታ ጊዜው ካለፈ በኋላ የቀረበ በመሆኑ አልተመረመረም በማለት የሰጠው የውሳኔ ክፍል ብቻ ተሽሯል፡፡ ሌላው የውሳኔ ክፍል ጸንቷል፡፡

3ኛ. የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የተዘጋውን መዝገብ አንቀሳቅሶ የአመልካችን መስቀለኛ የሰበር ቅሬታ መርምሮ ተገቢውን እንዲወስን ጉዳዩ ተመልሶለታል፡፡

4ኛ. በዚህ ፍርድ ቤት የተደረገው ክርክር ያስከተለውን ወጪ እና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/ተ

*ማ ስታወሻ፦ ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*